STAY SAFE MN



# የJohnson & Johnson የCOVID-19 ክትባት፥ማወቅ ያለብዎት ነገር

የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ማዕከል (CDC) በአሁኑ ሰዓት ከ Johnson & Johnson የCOVID-19 ክትባት ይልቅ mRNA የCOVID-19 ክትባቶች (Pfizer እና Moderna) ጥቅም ላይ እንዲውም ይመክራል።

## ምክረሃሳቦቹ ለምን ተሻሻሉ?

ባለሙያዎች የJohnson & Johnson COVID-19 ክትባት የሚያስከትለው የደም መርጋት የተወሰኑ የሞት አደጋን እንዳስከተሉ አረጋግጠዋል። ይህ ብዙ ጊዜ የማይከሰት ቢሆንም፣ በጣም አስጊ ሁኔታ ነው፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ስጋት የሌለባቸው ሌሎች ክትባቶች አሉ።




ባለሙያዎች Johnson & Johnson እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚሰራ እና ደህንነቱን በተመለከተ ወቅታዊ ጥናቶችን ከገመገሙ በኋላ ምክረ ሃሳቦችን አሻሽለዋል። ሁሉንም ክትባቶች ለደህንነት ሲባል መመርመራቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን፣ ካስፈለገም በዚያ ምርመራ ላይ ተመስርተው ምክረ ሃሳቦቻቸውን ያሻሽላሉ። ማንኛውም ያልተለመዱ ወይም ያልተጠበቁ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳት ምልክቶች ይመረመራሉ፣ ተደራሽ ይሆናሉ፣ እና ሰዎች እንዲያውቁት ይደረጋል።

## ከዚህ በፊት የJohnson & Johnson ክትባትን ከወሰድኩስ?

ክትባቱን ከወሰዱ ከወር በላይ ካለፈ ከJohnson & Johnson ክትባት ያልተለመደ የደም መርጋት ሊያጋጥምዎ የሚችልበት ሁኔታ ዝቅተኛ ነው።

**ከአንድ ወር በታች ከሆነ፣ እነዚህን ምልክቶች ይከታተሉ:**

- የትንፋሽ ማጠር
- የደረት ህመም
- የእግር ማበጥ
- የማይጠፋ የሆድ ህመም
- ከፍተኛ የራስ ህመም ወይም የማይጠፋ የራስ ምታት
- ብዥታ
- ከተወጋበት ቦታ ያለፈ ከቆዳ በታች በቀላሉ መበለዝ ወይም ትንሽ የደም ነጠብጣቦች

ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከነዚህ ምልክቶች አንዱ ካጋጠመዎት ወዲያውኑ የህክምና እርዳታ ማግኘት አለብዎት። በቅርቡ የJohnson & Johnson ክትባት እንደወሰዱ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢው ይንገሩ።



Johnson & Johnson የCOVID-19 ክትባት ከCOVID-19 ከባድ ህመም ይከላከላል፤ ነገር ግን፣ የ Johnson & Johnson ክትባት አንድ ክትባት የወሰዱ ሰዎች ክትባታቸውን መከታተል እና ለመጀመሪያ ጊዜ ከተከተቡ ከሁለት ወራት በኋላ አጋዥ ክትባት መውሰድ አለባቸው። ለአጋዥ ክትባት Pfizer ወይም Moderna ይመከራሉ።

# የተለየ ክትባት መውሰድ አለብኝ?

የመጀመሪያ ክትባትዎ Johnson & Johnson ከሆነ፣ በሌላ ክትባት እንደገና መጀመር አይጠበቅብዎትም።

የJohnson & Johnson አጋዥ ክትባት ከወሰዱ፣ በዚህ ጊዜ ሌላ ክትባት አያስፈልግዎትም።

አጋዥ ክትባት ካልወሰዱ፣ ከመጀመሪያዎ ክትባት ከሁለት ወር በኋላ አጋዥ ክትባት መውሰድ አለብዎት። ለአጋዥ ክትባት Pfizer ወይም Moderna ይመከራሉ።





**ራስዎን እና ሌሎችን ከCOVID-19 ለመጠበቅ ክትባት የተሻለው መንገድ ነው።**

ካልተከተቡ፣ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ ወይም በአቅራቢያዎ ባለ ቦታ ይከተቡ።

# የምፈልግ ከሆነ Johnson & Johnson ክትባትን መከተብ እችላለሁ?

ከፈለጉ አሁንም የJohnson & Johnson COVID-19 ክትባት መከተብ ይችላሉ። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ማንኛውም ሰው የደም መርጋት ሊያጋጥመው እንደሚችል ልብ ይበሉ። ነገር ግን፣ የደም መርጋት አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው ከ30-49 ዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ሴቶች ላይ ነው። ስለ ክትባቱ እና ሊያስከትላቸው ስለሚችለው ስጋቶች ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

## ራስዎን እና ሌሎችን ይጠብቁ

የCOVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ አሁናዊ የህዝብ ጤና ምክረሃሳቦችን መከተል መቀጠል አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሂደቶች ክትባቶች የCOVID-19ን ስርጭት ለመቀነስ የሚያደርጉትን ከባድ ስራ ይደግፋሉ፡



ጭምብል



ካመምዎት በቤትዎ ይቆዩ።



እጆችዎን ይታጠቡ።



ከሌሎች 6 የጫማ ርቀት ይራቁ።

MINNESOTA | mn.gov/vaccine

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975 | 651-201-5000

አማራጭ ፎርማት/ቅርጸት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ን ያነጋግሩ። (Amharic)

1/26/2022